# በሱና

## መብቃቃትና

# የቢድዐ

## ውግዝነት

### በነቢዩና በሰለፎች አንደበት

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች: ይከታተሉን።

## ረሱል صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّم እንዲህ ብለዋል፦

"ከኔ በፊት አላህ የላከው አንድም ነብይ የለም፣ ከህዝቦቹ ሱንናውን የሚይዙ፣ በትእዛዙ የሚገዙ ሐዋርያትና ባልደረቦች የኖሩት ቢሆን እንጂ፡፡ ከዚያም ከነሱ በኋላ ክፉ ምትኮች ይተካሉ፡፡ የማይሰሩትን ያወራሉ፡፡ ያልታዘዙትን ይፈፅማሉ፡፡ በእጁ የታገላቸው እሱ አማኝ ነው፡፡ በምላሱ የታገላቸውም እሱ አማኝ ነው፡፡ በልቡ የታገላቸውም እሱ አማኝ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የሰና-ፍጭ ፍሬ ታክል ኢማን የለም፡፡"

ሙስሊም ዘገበውታል: 50

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች: ይከታተሉን።

## ረሱል صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّم እንዲህ ብለዋል፦

# “የእኛ ትዕዛዝ የሌለበትን ስራ የሰራ ስራው ተመላሽ ነው፡፡”

ሙስሊም ዘግበውታል: 1718

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ረሱል صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّم እንዲህ ብለዋል፦

“ከዚህ በመቀጠል ‘ከንግግር ሁሉ በላጩ የአላህ መፅሐፍ ነው፡፡ ከመመሪያ ሁሉ በላጩ የሙሐመድ መመሪያ ነው፡፡ ከነገሮች ሁሉ መጥፎው መጤዎቹ ናቸው፡፡ ፈጠራ ሁሉ ጥመት ነው፡፡’”

ቡኻሪ: 7277 ሙስሊም: 867 ዘግበውታል

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን፡፡

## ረሱል صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፦

“ከኔ በፊት አንድም ነብይ አላለፈም፣ በሚያውቀው በጎ ነገር ህዝቦቹን ያመላከተ እንዲሁም ከሚያውቀው መጥፎ ነገር ያስጠነቀቃቸው ቢሆን እንጂ፡፡”

ሙስሊም ዘግበውታል: 1814

## ከዒርባድ ቢን ሳሪያ رضي الله عنه ተይዞ: እንዲህ ይላል፦

## ረሱል صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፦

“የአላህ መልዕክተኛ ልቦች በፍርሃት የራዱበት፣ አይኖች እንባ ያፈገፉበት የሆነን ምክር መከሩን፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ይህቺ ነገር የተሰናባች ምክር ትመስላለች ምን አደራ ትሉናለህ? አልናቸው በዚህን ግዜ እንዲህ አሉ፦ ‘ሌሊቱ ልክ እንደ ቀኑ በሆነ ግልፅ ፍኖት ላይ የተውኳችሁ፡፡ በሷ ላይ ጠፊ የሆነ እንጂ ከኔ በኋላ አያዘነብልም፡፡ ከናንተ የሚቆይ ሰው ብዙ ውዝግቦችን ያያል፡፡ ያኔ ባወቃችሁት ሱናዬና ከኔ በኋላ ያሉ ቀጥተኛና የተቀኑ የሆኑ ምትኮቼንም ሱና አደራችሁን፡፡’”

ሲልሲለቱ አሶሂሃ: 937

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ሰልማን አልፋሪሲ ﵁ ነቢያችሁ ﷺ

## የሽንት ቤት አጠቃቀም ሳይቀር ሁሉንም ነገር አስተምሯችኋል የሚል ነገር ሲነሳስቸው እንዲህ አሉ፦

‘እንዴታ! ለሰገራ ለሽንት ወደ ቂብላ እንዳንቀጣጭ በቀኛችን እንዳንፀዳዳ ከሶስት ድንጋዮች ባነሰ እንዳንፀዳዳ ወይም ደግሞ በፋንዲያ ወይም ደግሞ በአጥንት እንዳንፀዳዳ ከልክለውናል፡፡’

ሙስሊም ዘግበውታል: 262

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ያከታተሉን።

## ሑዘይፈቱ ብኑል የማን ﵁ እንዲህ ይላል፦

“የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ሶሐቦች ያላመለኩበትን እያንዳንዱ አምልኮ አላህን አታምልኩበት፡፡ የመጀመሪያዎቹ ለኋለኞቹ የተዉት ዘርፍ የለምና፡፡”

አዙህድ: 47

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ዐሊይ ብኑ አቡ ጧሊብ ﵁ እንዲህ ይላል፦

# “ዲን (እምነት) በግላዊ አስተያየት ቢሆን ኖሮ

**የስረኛው የእግር ክፍል ከላይኛው ይልቅ ሊታበስ ይገባው ነበር። ነገር ግን የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ሲያብሱ ያየሁት የላይኛውን ክፍል ነው።”**

አልሙሶነፍ ኢብኑ አቢ ሸይባህ: 183

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ዐብደሏህ ቢን መስዑድ ﷺ እንዲህ ይላል፦

“‘በሱና ላይ መብቃቃት በቢድዐ ላይ ከመታገል የበለጠ ነው።’ ወደ ጀርባቸው የወረወሩት ሆነው ሳለ ወደ አሏህ ኪታብ እንደሚጠሯችሁ የሚሞግቱ ሰዎች ታገኛላችሁ። በእውቀት ላይ አደራችሁን። ከቢድዐ፣ ከፀጉር ስንጠቃና ከመፈላፈል ተጠንቀቁ። ጥንታዊውን ነገር አደራችሁን ያዙ። ተከተሉ! አትፍጠሩ። በርግጥም (በመደንገግ ጉዳይ ላይ) ተብቅታችኋል።”

ሱነን ዳሪሚ: 236፣ 153፣ 224

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ኡበይ ኢብኑ ከዕብ رضي الله عنه እንዲህ ይላሉ፦

“በትክክለኛ መንገድና በሱንና ላይ መካከለኛ መሆን ከመንገዱ እና ከሱንና ውጭ ከመትጋት በላጭ ነው፡፡ ስለሆነም ስራችሁ ትጋትም ኖረበት መካከለኛም ሆነ በነብያት መንገድና በሱናዎቻቸው ላይ መሆኑን ተመልከቱ፡፡”

አለለካኢይ፡ 1/54

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## አልኢማም አልአውዛዒ رحمه الله እንዲህ ይላሉ፦

**“እራስህን በሱናህ ላይ አፅና፡፡ ሰዎቹ (ሶሐቦች) ከቆሙበትም ቁም፡፡**

**እነሱ ያሉትን በል፡፡ እነሱ ከታቀቡት ታቀብ፡፡ የመልካም ቀደምቶችህን መንገድ ተከተል፡፡ ለነሱ የበቃቸው ይበቃሀልና!!!”**

ካሺፉልጉማህ፡ 58

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ኢማሙ ማሊክ رحمه الله እንዲህ ይላሉ፦

“በኢስላም ውስጥ አዲስ ቢድዓን ፈጥሮ ያ ቢድዐ መልካም ናት ብሎ የሞገተ **በርግጥም የአላህ መልእክተኛ ተልእኳቸው ላይ ሸፍጥ ሰርተዋል ብሎ ሞግቷል።** ምክንያቱም አላህ እንዲህ ብሏል፦ ‘ዛሬ ለናንተ ሀማኖታችሁን ሞላሁላችሁ’ **ያኔ ዲን ያልነበረ ዛሬ ዲን አይሆንም።**”

አልኢዕቲሷም: 1/28

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ዑመር ኢብኑ ዐብዲል ዐዚዝ رَحِمَهُ ٱللَّهُ እንዲህ ይላሉ፦

"ሰዎቹ (ሶሐቦች) ከቆሙበት ቁም፡፡ እነሱ ከእውቀት ነው የቆሙት፡፡ ከጥልቅ ግንዛቤም ነው የታቀቡት፡፡ በርግጥም እነሱ ከናንተ በበለጠ እሷን (መጤዋን) በመግለጥ ብርቱ ነበሩ፡፡ በሷም ሳይ ትሩፋት ቢኖር ይበልጥ የተገቡ ነበሩ፡፡ 'ከነሱ በኋላ ነው የተፈጠረው' ካላችሁ መመሪያቸውን የጣሰ፣ ከሱንናቸው የዞረ እንጂ አልፈጠረውም፡፡ ከእውቀት፡ የሚያረካን ግልፅ አድርገዋል፡፡ በቂ የሆነንም ተናግረዋል፡፡ ከነሱ በላይ የሚጥር ከንቱ ደካሚ ነው፡፡ ከነሱ ያሳጠረ ወደኋላ የቀረ ነው፡፡ የሆኑ ሰዎች ከነሱ ቀሩና ራቁ፡፡ ሌሎች ከነሱ አለፉና ወሰን አለፉ፡፡ እነሱ ግን እዚህ መሀል ሳይ ቀጥ ካለ ቅናቻ ሳይ ናቸው፡፡"

ሉምዐቱል ኢዕቲቃድ፡ 8-9

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን፡፡

## ኢማሙ ማሊክ رحمه الله እንዲህ ይላሉ፦

# “የዚች ሕዝብ መጨረሻ አይስተካከልም። የመጀመሪያዋ በተስተካከለችበት ቢሆን እንጂ። ያኔ ዲን ያልነበረ ዛሬ ዲን አይሆንም።”

አልኢዕቲሷም: 1/115

@BuhariMuslimAmharic
በዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ኢማሙ አሕመድ رَحِمَهُ اللهُ እንዲህ ይላሉ፦

# “እኛ ዘንድ የሱንናህ መሰረቶች የአላህ መልእክተኛ ﷺ ሶሐቦች በነበሩበት አጥብቆ መያዝ፣ እነሱን መከተል፣ ቢድዐዎችን መተው ነው። እያንዳንዷ ቢድዐህ ጥመት ነች።”

ኡሱሉስሱንናህ አሕመድ: 1

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

ሶፊያን ሠውሪ رحمه الله እንዲህ ይላሉ፦

# “ቢድዐ ሸይጧን ዘንድ ከወንጀል ይበልጥ የተወደደ ነው።”

ዘሙል ከላም: 5/121

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

አዩብ አስሰኽቲያኒ رحمه الله እንዲህ ይላሉ፦

# “የቢድዐ ባለቤት ትጋት አይጨምርም፣ ከአላህ ርቀት ቢጨምር እንጂ፡፡”

ሒልየቱል አውሊያእ፡ 9/3

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## አዩብ አስሰኽቲያኒ رحمه الله እንዲህ ይላሉ፦

# “በሱንናና ላይ ያለ ጥቂት ስራ **በቢድዐ ላይ ካለ ብዙ ስራ ይበልጣል፡፡**”

ጃሚዑ በያኒል ዒልም፡ 2/1204

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ኢብኑ ተይሚያ رحمه الله እንዲህ ይላሉ፦

# “ብልጫ የሚገኘው በልፋት ብዛት አይደለም። ነገር ግን ቅናቻ እና ትክክለኛ መስመርን በመጓዝ ነው።”

መጅሙዑል ፈታዋ፡ 5/299

@BuhariMuslimAmharic

በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።

## ሸይኹል አልባኒ رحمه الله እንዲህ ይላሉ፦

# “ቁም ነገሩ አምልኮ (ዒባዳ) በማብዛት ሳይሆን ከቢድዐ ርቆ ሱና ላይ በመሆኑ ላይ ነው።”

አስሶሒሐህ፡ 2005

## ኢብኑ ሙባረክ رَحِمَهُ ٱللَّهُ እንዲህ ይላሉ፦

"እወቅ ወንድሜ! ዛሬ ለእያንዳዱ በሱና ላይ ሆኖ አላህን ለሚገናኝ ሰው ሞት ክብር ነው። ኢናሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂዑን! ስለ ባይተዋርነታችን፣ ስለ ወንድሞቻችን ማለቅ፣ ስለ ረዳቶች መቅለል፣ ስለ ቢድዐ መንገስ ወደ አላህ አቤት እንላለን። በዚህ ህዝብ ላይ የሱና ዑለማዎች በማለቃቸውና ቢድዐ በመንገሱ ሳቢያ ስለደረሰው ከባድ ፈተና ወደ አላህ አቤቱታችንን እናሰማለን። በከባድና ትልቅ ፈተና ባለበት ዘመን ውስጥ ነው ያለነው የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ያለንበትን ነገር ፈርተውልንና አስጠንቅቀውን ነበር አቡ ሁረይራ ባስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ ﷺ 'እንደ ድቅድቅ ሌሊት ቁራጭ የሆኑ ፈተናዎች መጡባቸው። በዚያ ውስጥ አንድ ሰው ሙዕሚን ሆኖ አንግቶ ከሀዲ ሆኖ ያመሻል። ሙዕሚን ሆኖ አምሽቶ ከሀዲ ሆኖ ያነጋል። ሰዎች በነዚህ ፈተናዎች ውስጥ ዲናቸውን በዱኒያ ሸቀጥ ይሸጣሉ።' ብለዋል።"

አልቢድዐ፣ ኢብኑ ወዷሕ: 159

@BuhariMuslimAmharic
በነዚህ አድራሻዎች ይከታተሉን።